# የዶ/ር ቀንጅት ፈቃደ ዜና እረፍት



ከወጣትነታቸው ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተደረገው የፍትህ ፡ የነጻነትና የእኩልነት ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት ዶ/ር ቀንጅት ፈቃደ ባደረባቸው ህመም ምክንያት ትላንት ታህሳስ 17 ቀን ከዚህ አመት በሞት ተለይተዋል። ዶ/ር ቀንጂት በምህንድስና ትምህርት የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪያቸውን በአሜሪካን ሀገር በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ከተመርቁ በሃላ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በተመራማሪነት ሰርተዋል። በሙያቸው ካደረጉት አስተዋጻኦ በተጨማሪ ሁልጊዜም የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተኛል በማለት ሳይታክቱ ለአገራቸው ሰላምና ለህዝቡ መብት መከበር ክፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ወደ አገራቸው እንደተመለሱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርነት ፡ በኢትዮጵያ ሰበአዊ መብቶች ጉባኤ(አሰመጉ)የቦርድ አባል በመሆን ፡ በሴቶች መብትና በሚዲያ ነጻነት ዙሪያ ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመስራት ክፍተኛ አስተዋጻኦ አበርክተዋል። ዶ/ር ቀንጅት ሁልጊዜም ለፍትህ የቆሙ ፡ የማናቸውም የሰው ልጅ በደል የሚያማችው፣ ማንም ኢትዮጵያዊ ተቸግሮ ማየት የማይፈልጉ ፡ ለሚያምኑበት ነገር በወሬ ሳይሆን በተግባር የቆሙ ቆራጥ አትዮጵያዊ ወገናችን ነበሩ። የዶ/ር ቀንጂት በለጋ እድሜ መቀጠፍ ለፍትህ የቆሙ ወገኖችን ቅስም የሰበረ አሳዛኝ ክስተት ነው።

የዶ/ር ቀንጂት የጸሎት ስነስረዓት የፊታችን እሮብ ታህሳስ 20 ቀን 2003 (December 29, 2010) አ.ም. በዋሽንግተን ዲሲ ይካሄዳል። የቀብር ስነ ስረዓታቸው የሚፈጸመው አገራቸው ውስጥ መሆኑን ቤተሰቦቻቸው አስታውቀዋል። ዶ/ር ቀንጅት የአንድ ወንድ ልጅ እናት ነበሩ።